*ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ*

***Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)***

***http://www.kinijitethiopia.org***

e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974

*ጋዜጣዊ መግለጫ* **ኪል-019-07**

**ሰኔ 9 ቀን፣ 1999**

# ከቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ

# የህዝባዊ እምቢተኝነት ዝግጅት ጥሪ

**ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ**

የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት የናፈቀውን ነጻነት፣ ዴሞክራሲና ሰላም፣ የተመኘውን ብልጽግናና እድገት አገኛለሁ ይሚላልኛል ብሎ ተስፋ ከማድረግ ተቆጥቦ አያውቅም፡፡ ይህን ተስፋውንና ምኞቱን የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት አጨልሞበታል፡፡ ይልቁንም፣ ለባሰ መከራና ስቃይ ርሃብና ስደት እስርና እርዛት ዳርጎታል፡፡

ያገኘውን እድል ተጠቅሞ፣ በምርጫ ስርአት ተማምኖና ያመነበትን ፓርቲ መርጦ፣ በብሩህ ተስፋና ምኞት ሚሊኒየሙን ለመቀበል እርቅንና ሰላምን፣ መግባባትና መደማመጥን፣ መከባበርና መተጋገዝን መጡልኝ አገኘኋቸው ብሎ ሲጓጓ፣ ተስፋው ጨልሞበታል፡፡ በሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ያለፍትህ በፖለቲካ ቁርሾ በተለያዩ የአገሪቱ ግዛቶች በእስር ያንገላታል፡፡ ይባስ ብሎ የፍትህ ስርአቱን የፖለቲካ መጠቀሚያ ከማድረግ አልፎ የእልህና የበቀል መወጫ እንዲሆን በሎሌዎቹ አማካኝነት፣ የህዝብ ተመራጮችን እና የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ህጋዊ የአቤቱታ መብት ነፍጎ በማናለብኝነት ሊፈርድባቸው ተዘጋጅቶአል፡፡

ህዝብን፣ በሚጎነጉነው ሴራ እርስ በርሱ በሃይማኖትና በዘር እየከፋፈለ በተለያየ የሃገሪቱ ግዛት በማበጣበጥ ላይ ይገኛል፡፡ ወታደሩንና ሰራዊቱን በዘር በመከፋፈል እርስ በርሱ እንዳይተማመን፣ የጦር መኮንኖችን በዘረኝነት ላይ በተመሰረተ መስፈርት በማሰር፣ በማባረር፣ በመግደልና አመራሩን ፍጹም የአንድ ወገን ደጋፊ ብቻ በማድረግ፣ ውጥረት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

እስካሁን በሰላማዊ መንገድ ለውጥን ለማምጣት እየተደረገ ያለውን ጥረትና የሰላማዊ ብሄራዊ እርቅ ጥሪን፣ በማናለብኝነት የሽንፈት ምልክት አድርጎ ወስዶታል፡፡ የህዝቡን የመናገር፣ ሃሳብ የመግለጽ፣ የመሰብሰብና የመደራጀት ነጻነት ነፍጓል፡፡ የዜጎችን ኢንፎርሜሽን የማግኘት መብት በመላው አለም ተወዳዳሪ በሌለው ሁኔታ አፍኖ ይዞአል፡፡ ወጣቱ ለስደት ለፍርሃትና ለውርደት ተዳርጓል፡፡ ገበሬው በከፍተኛ የአስተዳደር በደል ከመሰቃየቱም በላይ ተቃዋሚውን ደግፏሃል፣ የዚህ ወይም የዚያ ቡድን አባል ነህ፣ እየተባለ ይገረፋል ይታሰራል ይሰደዳል ይሰቃያል፡፡ይህ ሁሉ ሰቆቃና ስቃይ የሚደርሰው የዲሞክራሲና የሰብአዊ፣ የዜግነትና ህገመንግስታዊ መብት የሚጣሰው፣ ህዝብን ከመናቅና ከማናለብኝነት በመነጨ ትእቢት በመወጠር ነው፡፡

**የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!**

***የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን የትእቢት ውጥረት የሚያስተነፍስበት ጊዜ ደርሶአል፣ በመሆኑም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሚቀርበው ጥያቄ መሰረትና የወቅቱንም የወያኔ/ኢህአዴግ እርምጃዎች በመቃወም አጠቃላይ ህዝባዊ ተቃውሞና የእምቢተኝነት እንቅስቀሴ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ ይህ አገር አቀፍ እንቅስቃሴ፣ አጋር ድርጅቶችንና የዲሞክራሲ ሃይሎችን ያካተተ ሆኖ መላው የህብረተሰባችን ክፍል የሚሳተፍበት ይሆናል፡፡ ዝርዝር የተቃውሞ እርምጃዎችና አፈጻጸሞች እንደአግባቡ ለህዝብ ይገለጻሉ፡፡ ይህ ታውቆ የኢትዮጵያ ህዝብ ለሰላማዊ ትግሉና ለህዝባዊ እንቢተኝነት እንቅስቃሴ እራሱን አዘጋጅቶ እንዲጠብቅ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡***

***ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ***